# የማመልከቻዎን መልስ እየጠበቁ እያሉ

## ተጨማሪ ምርመራዎች ማድረግ ካለብን

ጉዳይዎን አስመልክቶ ተጨማሪ ምርመራዎች ማድረግ ካለብን መልስ እስኪያገኙ ድረስ ብዙ ሊውስድ ይችላል። ተጨማሪ ምርመራዎች ማድረግ ማለት ለምሳሌ  ሰነዶችዎን በዝርዝር ማጥናት ሲኖርብን ወይም ማንነትዎን አስመልክቶ በበለጠ ማጣራት ሲኖርብን እንደማለት ነው። ሌሎች ምርመራዎች እንደማለትም ይሆናል።  የውጪ ጉዳይ ሚንስተር [UDI] በሌሎች መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እርዳታ ላይ ይወሰናል። ስለሆነም በዚህ ምክንያት ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

እየጠበቁ የሚቆዩት ጊዜ በኖርዌይ የመኖር ፈቃድ ማግኘት ወይም አለማግኘት ላይ ምንም ተጽዕኖ የለውም። በሚቆዩበት ካምፕ/መቀበያ ቦታ ያሉት አንዳንዶቹ ከእርስዎ ቀድመው መልስ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ማለት ከየእርስዎ ማመልካቻ ጋር በተገናኘ ችግር አለ ማለትም አይደለም፣ ወይም የውጪ ጉዳይ ሚንስተር እርስዎን ረስቶዎት ነው ማለትም አይደለም። ምክንያቱ እኛ ስራዎችን የሚናቀናጅበት መንገድ ጋር ይዛመዳል።

ጉዳይዎን ሰርተን ሲንጨርስ ከኛ መልእክት ያገኛሉ።

## በጉዳየ ላይ የውጪ ጉዳይ ሚንስተር ውሳኔ ለመስጠት የሚውስድበት ጊዜ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ እችላለሁን?

በጉዳይዎ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚወስድብን ጊዜ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ አይችሉም።

መልስ ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ መጠበቅ እንዳለብዎት ለማወቅ ቢደውሉ የሚያገኙት መልስ በመረጃ ማጻጽፍ ላይ የተሰጠው የመጠበቂያ ጊዜዎች መረጃ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል። ከዚያ ውጪ የሚጠብቁት ጊዜ ምን ያክል እንደሆነ ልንነግርዎ አንችልም።

የውጪ ጉዳይ ሚንስተር ጉዳይዎ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ መጠበቅ የማይችሉ ከሆነ ወደ አገርዎ ለመመለስ ወይም የመኖር ፈቃድ ወደ ያለዎት ሌላ አገር ለመሄድ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

መመለስ የሚችሉበትን ድጋፍ ለማግኘት የሚያመለክቱበትን እንዲሁም የሚያገኙት ድጋፍ ምን ያክል እንደሆነ ለማወቅ በwww.udi.no/retur ያንብቡ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የስደተኝነት ዓለም አቀፍ ድርጅትን (IOM) በተሌፎን ቁጥር 23 10 53 20 ይጠይቁ ወይም በwww.iom.no ይመልከቱ።

UDI

**Les mer på**

[url]

**Skrevet av**

[Navn], [Navn]

## የመታወቂያ ወይም የሐኪም የምስኪር ወረቀት ወደኛ ስለመላክ

## የመታወቂያ ወረቀት የሚላከው ወደ ፖሊስ ነው

የመታወቂያ ወረቀት ለማግኘት የምቻልዎትን ማድረግ ቢችሉ በጣም ጥሩ ነው። ወደ የውጪ ጉዳይ ቢሮ የሚልኩት ዋናውን አይደለም፣ ለሚኖሩበት አካባቢ ፖሊስ ነው የሚያሰረክቡት። አለዚያም ሰነዶችዎን በፖስታ ለየፖሊስ የውጪ ጉዳይ ክፍል በዚህ አድራሻ ይልካሉ።

አድራሻው ይህ ነው።

[Politiets utlendingsenhet
v/Dokumentsenteret
Postboks 2095 Vika
0125 Oslo]

ስምዎንና የ[DUF]- ቁጥርዎን በወረቀት ላይ ጽፈው ፖስታው ውስጥ ማድረግ አለብዎት።

## የሐኪም የምስኪር ወረቀት የሚላከው ለየውጪ ጉዳይ ቢሮ ነው

ለማመልከቻዎ ጥቅም ያለው የጤና ችግር ካለብዎት፤ የሐኪም የምስኪር ወረቀት ከሐኪምዎ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። የሐኪም የምስኪር ወረቀቱን ለየውጪ ጉዳይ ቢሮ ይልካሉ።

አድራሻው ይህ ነው።

[UDI
Postboks 2098
0125 Oslo]

ስምዎንና የ[DUF]- ቁጥርዎን በወረቀት ላይ ጽፈው ፖስታው ውስጥ ማድረግ አለብዎት።

## በኢ-ፖስታ የሚላክ መረጃ

የስደተኝነት ማመልከቻዎን አስመልክቶ መረጃ በኢ-ፖስታ ያገኛሉ። የኢ-ፖስታ መልእክቱ የሚላከው በሰጡን የኢ-ፖስታ አድራሻ ነው።

ከኛ የሚያገኙት የመጀመሪያው መልእክት እኛ ጉዳይዎን ከፖሊስ ሲናገኝ ነው። ከዚያ በኋላ ሌሎች ዓይነት መልእክቶችንም እንልካለን። ለምሳሌ ጉዳይዎ በሂደት ላይ መሆኑን ወይም ጉዳይዎን አስመልክቶ ውሳኔ ላይ መድረሳችንን።

የሚላኩልዎት መልእክቶች የሚጻፉት በኖርዌጅኛና በእንግልዝኛ ይሆናል። እርስዎ ሰደተኝነት አመልካች ስለመሆንዎ ምንም መረጃ በሚላኩ ደብዳቤዎች/መልእክቶች ውስጥ አይጠቀስም።

የኢ-ፖስታ እንዲላክልዎት የማይፈልጉ ከሆነ ሊያሳውቁን ይገባዎታል። ለዚህ ለመመሪያ አሰጣጥ አገልግሎት በተሌፎን ቁጥር 23 35 16 00 መደወል ይችላሉ።